የሰ.መ.ቁ.239269

መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አበባ እምቢአለ

2. ብርሃኑ አመነዉ

3. በዕዉቀት በላይ

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ኑረዲን ከድር

አመልካች.....ወ/ሮ አበባ ካሳሁን

ተጠሪ..........አቶ አበራ አበጀ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የፍርድ አፈጻጸም ክርክር የተጀመረው በአማራ ክልል በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር የፍ/ባለዕዳ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር የፍ/ባለመብት ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.01-04408 በ10/04/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በአሁን ተጠሪ በፍ/ባለመብት እና በአሁን አመልካች በፍ/ባለዕዳ መካከል የብድር ገንዘብ መሰረት በማድረግ የተሰጠዉን ፍርድ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ተጠሪ ባቀረበዉ አቤቱታ አመልካች እንደፍርዱ ስላልፈጸመችልኝ እንድትፈጸምልኝ እንዲታዘዝልኝ በማለት መጠየቁትን ተከትሎ፣ በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኘዉ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ-3 B00714 አ.አ የሆነዉ ቪትስ መኪና በጨረታ ተሽጦ እንዲከፈለኝ በማለት የጠየቀ ሲሆን፣ የሥር ፍ/ቤት ይህ ተሽርካሪ በጨረታ ተሽጦ ለተጠሪ እንዲከፈለዉ ትዕዛዝ መስጠቱን መዝገቡ ያሳያል፡፡

ነገር ግን የአሁን አመልካች ባቀረበችዉ አቤቱታ የተወሰነብኝን የብድር ገንዘብ አብዛኛዉን ክፍያ የጨረስኩኝ ስለሆነ የተጠቀሰዉ መኪና እንዲሸጥ የወጣዉ ጨረታ እንዲሰረዝልኝና በመኪናዉ ላይ የተሰጠዉ እግድ እንዲነሳልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ ተጠሪ በዚህ አቤቱታ ላይ ባቀረበዉ ክርክር በዚህ ፍርድ አፈጻጸም ምክንያት የተከፈለኝ ገንዘብ የለም፣ ጨረታዉ ሊቋረጥ አይገባም በማለት የተከራከረ መሆኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡

ከዚህ በኋላ የማዕከላዊ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር ባሳለፈዉ ብይን አመልካች ለተጠሪ ገንዘብ ከፍያለሁኝ ትበል እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.396 (3) መሰረት በፍ/ቤት መዝገብ ያልተመዘገበ ክፍያ በፍርድ አስፈጻሚ ፍ/ቤት ዋጋ ሊሰጠዉ ስለማይችል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበችዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፤ ጨረታዉ የሚቋረጥበት አግባብ የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተዉ ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበች ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ በመሰረዝ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ በዚህ ብይንና ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

አመልካች በ21/4/2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ተጠሪ ያቀረበዉን የአፈጻጸም አቤቱታ ከመጥሪያ ጋር ሳይደርሰኝ አልቀበልኝ እንዳልኩኝ አስመስሎ በቃል መሐላ የመለሰዉ ቢሆንም አመልካች ከተወሰነብኝ ገንዘብ ዉስጥ በአጠቃላይ ብር 257000.00 በበተጠሪ የባንክ ሂሳብ ዉስጥ ገቢ ያደረኩኝ መሆኑን ማስረጃ አያይዤ አቅርቤ እያለሁኝ፣ ቀሪዉን ገንዘብ ደግሞ በሞዴል 85 በፍ/ቤት እንዳስይዝ እንዲታዘዝልኝ እየጠየቀኩኝ የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.396 ከሚደነግገዉ ዉጭ የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበሉ ቀርተዉ የአመልካች ንብረት በጨረታ እንዲሸጥ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልኝ በአመልካች መኪና ላይ የተጠሰዉ እግድ እንዲሁም የተጀመረዉ የጨረታ ሂደት እንዲሰረዝልኝና መኪናዉ እንዲለቀቅልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣አመልካች ያለባትን እዳ አብዛኛዉን በባንክ ለተጠሪ መክፈሏን ገልጻ እያለ ሳይጣራ መኪናዋ እንዲሸጥ ጨረታ የወጣበትን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በፍርዱ መሰረት አለመፈጸማቸዉን በማጣራትና በማረጋገጥ የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔ የሚነቀፍበት አግባብ ስለሌለዉ፣ የቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ስለለለዉ፣ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች በ14/6/2015 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዋን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በግራ ቀኛቸዉ መካከል በነበረዉ የብድር ገንዘብ ክርክር ፍ/ቤት አመልካች ያለባትን የብድር ገንዘብ ለተጠሪ እንዲትከፍለዉ መወሰኑን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ነገር ግን የአሁን ተጠሪ ለሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበዉ የአፈጻጸም አቤቱታ አመልካች በዚህ የፍርድ ዉሳኔ መሰረት ስላልፈጸመችልኝ እንደፍርድ እንዲትፈጸምልኝ በማለት ያመለከተ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም አመልካች በፍርዱ መሰረት የማትፈጽምበት ምክንያት ካለ ቀርባ እንዲታስረዳ መጥሪያ እንዲደርሳት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ በቃለ መሐላ በተደገፈ አቤቱታ አመልካች ፍ/ቤቱን መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ አይደለችም በማለት መጥሪያ ለፍ/ቤት በመመለሱ፤ ፍ/ቤቱም አመልካች እንደፍርዱ እንዲትፈጽም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.386 (3) መሰረት ትዕዛዝ መሰጠቱን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረት የሥር ፍ/ቤት ፍርዱን ለማስፈጸም ሲባል በአመልካች ስም የተመዘገበዉ ተሽከርካሪ እንዲታገድና በጨረታ እንዲሸጥ ትዕዛዝ መስጠቱን መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ይህን ተከትሎ አመልካች ባቀረበችዉ አቤቱታ ከተወሰነብኝ

ገንዘብ ዉስጥ አብዛኛዉን በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረኩኝ ስለሆነና ቀሪዉን ደግሞ በሞዴል 85 በፍ/ቤት እንዳስይዝ እንዲታዘዝልኝ፣ መኪናዉ እንዲሸጥ የወጣዉ ጨረታ እንዲሰረዝልኝ፣ በመኪናዉ ላይ የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳልኝ በማለት የጠየቀች ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር አመልካች በፍርዱ መሰረት የከፈለችኝ ገንዘብ የለም ብሎ በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር አመልካች በፍርድ የተወሰነባትን ገንዘብ ለተጠሪ ከፍያሉኝ ትበል እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.396 መሰረት ክፍያዉ በፍ/ቤት ስላልተመዘገበ የአመልካች ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም፤ የአመልካች መኪና በጨረታ እንዲሸጥ የተሰጠዉ ትዕዛዝ ሊሰረዝ አይገባም ጨረታዉ እንዲቀጥል በማለት መወሰኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡

እንደሚታወቀዉ የፍ/ባለዕዳ እንደፍርዱ የማይፈጽምበትን ምክንያት ቀርቦ ያላስረዳ እንደሆነ ወይም ያቀረበዉ ምክንያት በቂ ያልሆነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ፍርዱ እንዲፈጸም ወዲያዉኑ ትዕዛዝ እንደሚሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.386 (3) ድንጋጌ ሥር ተመልክቷል፡፡ ይህ ማለት ግን የአፈጻጸም ክርክሩ በቀጠለበት ሁኔታ የፍ/ባለዕዳዉ እንደፍርዱ ለመፈጸም ፈቃደኛ መሆኑን ቀርቦ ከመግልጽ የሚከለከል አለመሆኑን ወይም እንደፍርዱ መፈጸሙን ጠቅሶ ለፍ/ቤቱ አቤቱታ እንዳያቀርብ የሚከለከል አለመሆኑን ወይም ፍ/ቤቱ በምንም መልኩ የፍ/ባለዕዳዉ እንደፍርዱ ለመፈጸም ያለዉን ፈቃደኛነት መጠየቅ እንደማይችል የማያመለክት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.387-393 ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ መረደት እንደሚቻለዉ የፍርድ አፈጻጸም ክርክር ሂደት በቀጠለበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ የፍ/ባለዕዳዉ እንደፍርዱ ለመፈጸም ያለዉን ፈቃደኛነት የሚጠይቅበት አግባብ መኖሩን፤ የፍ/ባለዕዳዉም ፍርዱን ለመፈጸም ፈቃደኛ ከሆነ ይህንኑ ለፍ/ቤቱ መግለጽ የሚችል መሆኑን ወይም በፍርድ አግባብ የፈጸመ እንደሆነ ይህ ጉዳይ እንዲታይለት ለፍ/ቤት ማመልከት የሚችል መሆኑን እና ፍ/ቤቱም በዚህ አግባብ የቀረበዉን ጥያቄ መርምሮ ተገቢዉን ትዕዛዝ ከመስጠት እንደማይከለከል ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል ገንዘብ እንዲከፈል ፍርድ የተሰጠ እንደሆነ፣ የፍ/ባለዕዳዉን ንብረት በማስከበርና በመሸጥ ፍርዱን ማስፈጸም እንደሚቻል እና ይህ ንብረት ግን በተቻለ መጠን በዉሳኔዉ ከተገለጸዉ ገንዘብ ልክ ጋር ተመዛዛኝ መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.394 ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ እንዲሁም በዋናዉ ፍርድ የተወሰነዉ ገንዘብ የሚከፈልበት አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.394 ሥር የተመለከተ ሲሆን፣ ከዚህ ዉስጥ በፍርድ የተወሰነዉን ገንዘብ ከፍ/ቤት ዉጭ ለፍ/ባለገንዘቡ መክፍል እንደሚቻል ተደንግጓ እናገኛለን፡፡ በዚህ አግባብ በፍርድ የተወሰነዉ ገንዘብ ከፍ/ቤት ዉጭ የተከፈለ መሆኑን ፍ/ቤቱ ያረጋገጠ እንደሆነ ለፍ/ባለመብቱ እንደሚያሳዉቅ ያመለክታል፡፡ የፍ/ባለዕዳዉ በፍርድ የተወሰነዉን ገንዘብ ከፍ/ቤት ዉጭ ለፍ/ባለመብቱ የከፈለዉ መሆኑን ጠቅሶ ለፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ፣ ፍ/ቤቱም የፍ/ባለዕዳዉ አቤቱታ ለፍ/ባለመብት እንዲደርሰዉ በማድረግ፣ የፍ/ባለመብቱ እንደፍርዱ የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን እንዲያስረዳ እንደሚያደርግ እና የፍ/ባለመብት ይህን ሁኔታ ለፍ/ቤቱ ያላስረዳ እንደሆነ ይኸንኑ በመዝገብ ጽፎ እንደሚያሰፍር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.396 (1) (2) እና (3) ድንጋጌ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት በፍ/ቤቱ መዝገብ ያልተመዘገበ ክፍያ በማናቸዉም ፍርድ አስፈጻሚ ፍ/ቤት ዘንድ ዋጋ ሊሰጠዉ እንደማይችል ተደንግጓል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከዚህ ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ መረዳት እንደሚቻለዉ ገንዘብ እንዲከፍል ፍርድ የተሰጠ እንደሆነ፣ የፍ/ባለዕዳዉ የተወሰነበትን ገንዘብ ከፍ/ቤት ዉጭ ለፍ/ባለገንዘብ መክፈል የሚችል መሆኑን፤ የፍ/ባለዕዳዉ በዚህ አግባብ ገንዘብ ከፍሎ እንደሆነ ግን በዚህ መሰረት ክፍያ መፈጸሙን ለፍ/ቤቱ አቤቱታ በማቅረብ የፍ/ባለመብት ፍርዱ መፈጸሙን እንዳይመዘገብ የሚቃወምበት ምክንያት መኖሩን እንዲጠይቅለት ማመልከት እንደሚችል፤ ፍ/ቤቱም ይህን የቀረበዉን አቤቱታ መነሻ በማድረግ የፍ/ባለመብቱ ክፍያዉ መፈጸም አለመፈጸሙን ቀርቦ እንዲያስረዳ እንደሚያደርገዉ፣ እና ይኸንኑ በመዝገብ ማስፈር እንደሚገባዉ ያስገነዝባል፡፡ ይህ ማለት የፍ/ባለዕዳ የተወሰነበትን ገንዘብ ከፍ/ቤት ዉጭ ለፍ/ባለመብት ከፍያለሁኝ ተጣርቶ እንዲመዘገብልኝ በማለት የሚቀርበዉን አቤቱታ፣ ፍ/ቤቱ የፍ/ባለመብቱን አስተያየት ከጠየቀ በኋላ ተገቢዉን ማጣራት በማድረግ ትዕዛዝ እንደሚሰጥበት ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ በዚህ አግባብ የፍ/ባለዕዳዉ የተወሰነበትን ገንዘብ ከፍ/ቤት ዉጭ ለፍ/ባለመብት ከፍሎታል ወይስ አለከፈለዉም? ከፍሎት ከሆነ ቀሪ ገንዘብ አለ ወይስ የለም? የሚሉትን ነጥቦች ሳያጣራ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.396 (4) መሰረት ከፍ/ቤት ዉጭ የተከፈለዉ ገንዘብ በፍ/ቤት ያልተመዘገበ ስለሆነ ዋጋ ሊሰጠዉ አይገባም በማለት ትዕዛዝ የሚሰጥበት አግባብ አይኖርም ማለት ነዉ፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በግራ ቀኙ መካከል የአፈጻጸም ክርክር እየቀጠለ ባለበት ሁኔታ አመልካች ባቀረበችዉ አቤቱታ በፍርድ ከተወሰነብኝ ገንዘብ ዉስጥ አብዛኛዉን በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ገቢ አድርጌአለሁኝ እንዲሁም ቀሪዉን ገንዘብ በፍ/ቤት በሞዴል 85 መሰረት እንዳስቀምጥ እንዲታዘዝልኝ በማለት ያመለከተች ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር እንደፍርዱ የከፈለችኝ ገንዘብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ይህ ከሆነ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.396 መሰረት የግራ ቀኙን ክርክር መነሻ በማድረግ፣ አመልካች በፍርድ ከተወሰነባት ገንዘብ ዉስጥ ከፍ/ቤት ዉጭ በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገችዉ ገንዘብ አለ ወይስ የለም? ገቢ ያደረገችዉ ገንዘብ ካለ ምን ያህል ነዉ? እንዲሁም ቀሪ ገንዘብ ምን ያህል ነዉ? የሚሉትን ነጥቦች ከቀረበዉ ማስረጃ አንጻር አጣርቶ ተገቢዉን ትዕዛዝ ከመስጠት የሚከለክለዉ የሕግ አግባብ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት በዚህ አግባብ ጉዳዩን ካጣራ በኋላ አመልካች ለተጠሪ በፍርዱ መሰረት የከፈለችዉ ክፍያ መኖሩን ካረጋገጠ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.396 (4) መሰረት በመመዝገብ፣ ያልከፈለችዉ ክፍያ ካለ ደግሞ ተገቢ ነዉ ያለዉን ትዕዛዝ መስጠት ይገባዉ ነበር፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ይህን ጉዳይ በዚህ አግባብ አይተዉ ተገበዉን ትዕዛዝ መስጠት ሲገባቸዉ በፍ/ቤት ያልተመዘገበ ክፍያ ዋጋ ሊሰጠዉ አይገባም በማለት የሰጡት ዉሳኔ የሕጉን ይዘትና ዓላማ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በፍርድ ከተወሰነብኝ ገንዘብ ዉስጥ አብዛኛዉን ከፍ/ቤት ዉጭ ክፍያ ፈጽሜአለሁኝ፣ የቀረዉን ገንዘብ ደግሞ በሞዴል 85 በፍ/ቤት እንዳስቀምጥ እንዲታዘዝልኝ በማለት አመልክታ እያለች፣ ይህን ጉዳይ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ አግባብ አጣርተዉ ተገቢዉን ዉሳኔ ሳይሰጡት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ያሳለፉት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የማዕከላዊ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.01-51118 በ4/13/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.01-04408 በ10/04/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የማዕከላዊ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በብይን የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ አመልካች ያቀረበችዉን አቤቱታ እና በተጠሪ የተነሳዉን ክርክር መሰረት በማድረግ፣ አመልካች በፍርድ ከተወሰነባት ገንዘብ ዉስጥ ከፍ/ቤት ዉጭ በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገችዉ ገንዘብ አለ ወይስ የለም? ገቢ ያደረገችዉ ገንዘብ ካለ ምን ያህል ነዉ? እንዲሁም ቀሪ ገንዘብ ምን ያህል ነዉ? የሚሉትን ነጥቦች አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት ተመልሶለታል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤት የአመልካች ንብረት የሆነዉ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ-3 B00714 አ.አ የሆነዉ ቪትስ መኪና እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በማናቸዉም መንገድ ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ የሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ አልተነካም፡፡ ነገር ግን የሥር ፍ/ቤት በተራ ቁጥር 2 ሥር በተጠቀሰዉ አግባብ ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢዉን ዉሳኔ ሳይሰጥበት መኪናዉ በጨረታ እንዲሸጥ የሰጠዉ ትዕዛዝ ተገቢ ስላልሆነ የዚህ ዉጤት እስከሚታወቅ ድረስ መኪናዉ መያዝና በጨረታ መሸጥ ስለሌለበት ለአመልካች ይመለስ ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
6. ይህ ችሎት በ26/4/2015 ዓ.ም የሰጠዉ የአፈጻጸም እግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም